# የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ኢሰመጉ

**ኢሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!**

## አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ

## የኢትዮጵያ ወቅታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ፈጣን መፍትሔ ይሻል!

**ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም**

ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀቻቸውና የሕጎቿ አካል ያደረገቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ሰዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ፣ በማንኛውም ቦታ በሕይወት የመኖር ሰብዓዊ መብቶች እንዳሏቸው ይደነግጋሉ፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥትም ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ ብቻ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት እንዳለው በአንቀጽ 14 ሥር ይደነግጋል፡፡ ይሁንና፤ ከሰሞኑ በበርካታ የሐገራችን አካባቢዎች በተፈጠሩ ችግሮች ሰዎች የአካል ደህንታቸው ተጠብቆ በማንኛውም ቦታ በሕይወት የመኖር መብታቸው በልዩ ልዩ ምክንያቶች ተጥሷል፡፡

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግሥት፣ ቤንች ሸኮ ዞን፣ ጉራ ፈርዳ ወረዳ ጥቅምት 8 እና 9 ቀን 2013 ዓ.ም ማንነታቸው ለጊዜው ያልታወቁ አካላት ባደረሱት ድንገተኛ አደጋ የበርካታ ሰዎች ሕይወት ማለፉን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን እና ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል፡፡ ችግሩ ከተከሰተ በኋላ በመንግሥት በኩል በተወሰደ እርምጃ የመንግሥት አመራሮች እና የፖሊስ አባላትን ጨምሮ በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በምዕራብ ሸዋ፣ በምዕራብ ወለጋ እና በሆሮ ጉድሩ ዞኖች ውስጥ ባሉ አካባቢዎች ከሰሞኑ ማንነታቸው ለጊዜው ባልታወቁ አካላት እና በመንግሥት ፀጥታ ኃይሎች እርምጃ የሰዎች ሕይወት አልፏል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት በአካባቢዎቹ ይስተዋሉ የነበሩት የፀጥታና ደህንነት ችግሮች ከሰሞኑ ተባብሰው ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በነዋሪዎች ላይ ዓይነተ-ብዙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየደረሱ መሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል፡፡ የአካባቢው ሕዝብ በአንድ በኩል ትጥቅ አንግበው ጫካ የገቡ ቡድኖችን ትደግፋላችሁ፣ የእነሱም አባላት ናችሁ በሚል ወከባ እና እንግልት የሚደርስባቸው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የመንግሥት ደጋፊዎች ናችሁ፣ የመንግሥት አመራሮች ቤተሰብ ናችሁ በሚል በሁለት አቅጣጫ ከፍተኛ የሆነ እንግልት እየደረሰበት መሆኑን ኢሰመጉ በየሳምንቱ ከሚያደርጋቸው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ዳሰሳ ለመረዳት ችሏል፡፡

በሌላ በኩል፤ ማንኛውም ሰው መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታውን የማቅረብ መብት እንዳለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 30 ሥር ይደነግጋል፡፡ ከሰሞኑ ግን በአዲስ አበባ ከተማ፣ በአማራ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ቅሬታቸውን ለማሰማት ሰላማዊ ሰልፎችን ለማድረግ በሚሞክሩ ሰዎች እና የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች ላይ የሚደረገው ክልከላ፣ እስር እና የኃይል እርምጃ ተቀባይነት የሌለው ሕገ-ወጥ ድርጊት መሆኑን ኢሰመጉ ያምናል፡፡ ሁኔታዎች በዚህ መልኩ ከቀጠሉ

በዚህ ዓመት ሊደረግ የታሰበው ምርጫ በሚቃረብበት ወቅት ደግሞ ከዚህም የከፉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ አመላካች ነው፡፡

በመሆኑም፤ እነዚህ ችግሮች በተለይም በዚህ ዓመት ሊደረግ ከታሰበው ብሔራዊ ምርጫ ጋር ተዳምሮ፣ ከፍተኛ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ቀውስ እንዳያስከትል መንግሥት ፈጣን የሆነ ሕጋዊ የእርምት እርመጃዎችን እንዲወስድ ኢሰመጉ ያሳስባል፡፡ ኢሰመጉ መንግሥት ያለበትን ወቅታዊ ውስብስብ ሁኔታዎች እና የፀጥታ ኃይል አባላት እየተወጡ ያለውን ከባድ ኃላፊነት ግዝፈት የሚረዳ ቢሆንም፤ ይህን መሰሉን የሐገሪቱን አሳሳቢ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ግን የፌደራሉም ሆነ ችግሮች እየተፈጠሩባቸው ያሉ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የክልል መንግሥታት፣ ባለድርሻ ከሆኑ አካላት ጋር በጥልቀት በመወያየት ለችግሩ ዘላቂ እና ፈጣን መፍትሔ መስጠት የሚገባቸው መሆኑን ዳግም ለማሳሰብ ይወዳል፡፡

**ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም አቀፍ ጸረ-ሥቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣ የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ጥበቃ ኅብረት (Defend Defenders) መሥራች አባል ነው፡፡**